Physicians for Human Rights

Organization for Justice and Accountability in the Horn of Africa (OJAH)

# የተሰበሩ ቃልኪዳኖች፡- በግጭት ወቅት የተከሰቱ ጾታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች ከ”ተኩስ አቁም ስምምነት” በፊት እና በኋላ በኢትየጵያ ትግራይ ክልል ዉስጥ

## ማጠቃለያ

ሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ክልል ዉስጥ በኢትዮጵያ መንግስት እና በህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ሃይሎች እንዲሁም በኤርትራ ወታደራዊ ሃይሎች፣ በአማራ ክልል ልዩ ሃይሎች እና ሚሊሻ ቡድኖች ሰፊ ተሳትፎ የተካሄደዉ ጦርነት ዉስጥ የወሲብ ጥቃቶች [1] በሰፊዉ ታይተዋል። በህዳር 2015 ዓ/ም በኢትዮጵያ መንግስት እና በህወሀት መካከል ከተደረገዉ የጦርነት ማቋረጥ ስምምነት  ከመደረጉ በፊትም ሆነ በኋላ ከግጭት ጋር የተያያዙ ጾታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች የግጭቱ ዋና አካል እንደሆኑ የሚገልጹ ሪፖርቶች  ታይተዋል። [1-3] በኢትዮጵያ ከሚገኙ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና የህብረተሰብ ጤና ባለሙያዎች እንዲሁም ሃኪሞች ለሰብአዊ መብቶች ከተባለ የበጎ አደራጎት ድርጅት በተውጣጣ ጥምር የምርምር ቡድን የተካሄደዉ ይህ ጥናት ግጭቱ ከጀመረበት ከህዳር ወር 2013 ዓ/ም አንስቶ ጭካኔ የተሞላባቸዉ እና መጠነ ሰፊ የሆኑ ወሲባዊ ጥቃቶች በተለያዩ ወታደራዊ ሃይሎች እንደፈተጸሙ የሚያሳይ ሲሆን ፣ በነዚህ ሃይሎች በትግራይ ክልል ዉስጥ የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶች የተኩስ አቁም ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላም አላማቋረጣቸዉን ያመለክታል።
የሰብአዊ መብት ጥናትና ምርምር ቡድኑ በትግራይ ክልል ዉስጥ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የተፈፀመውን የግጭት-ነክ ጾታዊ እና ወሲባዊ ጥቃት ዓይነቶችን እና መገለጫዎችን በጥቂቱ ለመመርመር እና ለመመዝገብ በማቀድ ባካሄደዉ በዚህ ጥናት ዉስጥ በክልሉ ከሚገኙ የተለያዩ የጤና ተቋማት ከህዳር 2013 ዓ/ም እስከ ሰኔ 2015 ዓ/ም ደረስ አገልግሎት ካገኙት የጥቃቱ ሰለባዎች የተሰበሰቡ የህክምና መዝገቦች ዉስጥ የተወሰኑትን ማለትም በቁጥር 305 የሚሆኑ መዝገቦችን በመገምገም እድሜያቸዉ ከ 8 አመት እስከ 69 አመት የሚሆኑ ሴቶች እና ህጻናት ላይ ከፍተኛ     ቁጥር ያላቸዉ የወሲብ ጥቃቶች መፈጸማቸዉን አሳይቷል።

### *ቁልፍ ግኝቶች*

የተጠኑት የሕክምና መዝገቦች በመንግስት ታጣቂ ሃይሎች በጦርነቱ ወቅት የደረሱትን ስልታዊ እና መጠነ ሰፊ የሆነ የወሲብ ጥቃት አሰቃቂነት ያሳያሉ። ሁሉም የግጭቱ ተሳታፊ አካላት ጾታዊ ጥቃቶችን ካለመከላከላቸዉ እና ካለማስቆማቸዉ በተጨማሪ ሰለባዎች የደረሰባቸዉን ጥቃት ሪፖርት እንዲያደርጉ እንዲሁም በእነዚህ ድርጊቶች ለደረሰባቸው አስከፊ ጉዳት የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ አልቻሉም።

**ጾታዊ ጥቃቶቹ አብዛኛዉን ጊዜ የተፈጸሙት በቡድኖች ሲሆን አንዳንዶቹ ጥቃቶችም እስራትን እና የጦር መሳሪያዎችን በመጠቀም ማስፈራራትን እንደሚጨምሩ ጥናቱ ያመላክታል ።** በጥናቱ ዉስጥ የተካተቱት ሰነዶች እንደሚያመላክቱት አብዛኞቹ (76%) የአስገድዶ መድፈር ጥቃቶች የተፈጸሙት ቁጥራቸዉ ከአንድ በላይ በሆኑ ወንዶች ህብረት (በአማካኝ ሶስት) ሲሆን  የተቀሩት ደግሞ በአንድ ግለሰብ የተፈፀሙ አስገድዶ መድፈር ጥቃቶቸ ናቸዉ። አንዳንድ የወሲብ ጥቃት ሰለባዎች በአጥቂዎቹ ለእስራት እንደተዳረጉ እና ከወሲባዊ ባርነት ጋር በሚመሳሰል መልኩ ለረዥም ጊዜ አግተዉ በተደጋጋሚ አስገድደዉ እንደደፈሯቸዉ ከ10 በማያንሱ መዝገቦች ዉስጥ ተሰንዶ ተገኝቷል። ቀላል የማይባሉ ወንጀለኞች ከጾታዊ ጥቃቶቹ ጎን ለ ጎን የጦር መሳሪያዎችን አለያም ሌላ አይነት መሳሪያዎችን በመጠቀም አካላዊ ጥቃቶችን ያደረሱ ሲሆን የጥቃቱ ሰለባዎች በድርጊቱ ወቅት ልጆቻቸዉን ጨምሮ ሌሎች የቤተሰብ አባላቶቻቸዉን ጥቃት ፈጻሚዎቹ እንደገደሉባቸዉ በርካታ የህክመና መዘገቦች ያሳያሉ።

**አብዛኛዎቹ ወንጀለኞች የኤርትራ ወይም የኢትዮጵያ ታጣቂ ሃይሎች እንደሆኑ የአስገድዶ መድፈር ሰለባዎቹ ገልጸዋል።** አብዛኛዎቹ ማለትም 66% የሚሆኑት ወንጀለኞች የትግርኛ ቋንቋ ይናገሩ እንደነበረ የጥቃቱ ሰለባዎች ገልጸዋል። መዝገቦቹ ላይ እንደተሰነደዉ 96% ወንጀለኞች የወታደራዊር ወይም የተለያዩ ታጣቂ ሃይሎች አባላት ሲሆኑ ሁሉንም በሚባል ደረጃ ማለትም 99% የሆኑትን ወንጀለኞች ታካሚዎቹ ከዚህ ቀደም አይተዋቸዉ እንደማያውቁ ተናገረዋል። የያንዳንዱን ወንጀለኛ ዩኒፎርም፣ መለዮ እንዲሁም የአነጋገር ዘዬ መለየት ባይቻልም በቁጥር 143 በሚሆኑ የአስገድዶ መድፈር ጥቃቶች ላይ ከተሳተፉት ወንጀለኞች ዉስጥ ቢያንስ አንዱ የኤርትራ ወታደር እንደነበር ሲገለጽ በጦርነቱ ወቅት የኤርትራ እና የኢትዮጵያ ሃይሎች በጥምር ይዋጉ እንደነበር የሚታወስ ነዉ[8]። የጥቃቱ ሰለባዎች እንደገለፁት 30% የሚሆኑት ጥቃቶች የተፈጸሙት አማርኛ በሚናገሩ ሰዎች ሲሆን አስራ ስድስት የሚሆኑት ደግሞ የኢትየጲያ መከላከያ ሃይል አባሎች ነበሩ።

**ሰላማዊ ዜጐች ከግጭት ጋር በተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች ምክንያት ለባድ የጤና ችግር ቢጋለጡም ድርጊቱን ሪፖርት ከማድረግ እና የሕክምና እንክብካቤ ከማግኘት ግን እንዲዘገዩ ተገደዋል።** የተጠኑት የሕክምና መዛግብት ታካሚዎቹ

በደረሰባቸዉ የወሲብ ጥቃቶች ምክንያት የተለያዩ የረጅም ጊዜ እና የአጭር ጊዜ አካላዊ እና አእምሮአዊ ጉዳቶች እንደደረሰባቸዉ ሲያሳዩ የአእምሮ ጭንቀት፤ድብርት፣ድባቴ፣ያልተፈለገ እርግዝና እንዲሁም ከልክ ያለፈ የማህጸን ደም መፍሰስ፣ ሽንት እና ሰገራን መቆጣጥር አለመቻል እና ፊስቱላ የመሳሰሉ የመራቢያ አካላት ጉዳቶች በሰፊው ታይተዋል። በህክምና ወቅት የእርግዝና ምርመራ ከተደረገላቸዎ ዉስጥ 27% የሚሆኑት ማርገዛቸዉ ሲረጋገጥ [2] የኤች አይ ቪ ምርመራ ከተደረገላቸዉ ዉስጥ 11% የሚሆኑት ደግም በደማቸው ዉስጥ ቫይረስ መገኘቱ ተረጋግጧል[3] ።ተጠቂዎች ከደረሰባቸዉ ጉዳት ለማገገም የሚያሰፈልጋቸዉን የሕክምና እንክብካቤ በአስፈላጊዉ ጊዜ ማግኘት አለመቻላቸዉን መረጃዉ ያሳያል። የጥቃቱ ሰለባዎች ወደ ጤና ተቋማት የሄዱት በአማካይ የአምስት ወራት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ነበር። ምንም እንኳን መዘግየቶቹ ሙሉ ለሙሉ ለምን እንደተፈጠሩ ግልጽ ባይሆንም መገለል፣ በደህንነት ፍርሃት፣ ቀጣይነት ያለው ግጭት በትራንስፖርት አለመኖር እና የጤና ተቋማት መዘጋት እንደምክኒያት ሊጠቀሱ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት መዘግየቶች በጦርነቱ ወቀት የደረሱ ወሲባዊ ጥቃቶች በአብዛኛዉ ሪፖርት አለመደረጋቸዉን ያመላከታል።

**ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲብ ጥቃቶች የተኩስ አቁም ስምምነቱን ተከትሎም አልቆመም።** የተገመገሙት የሕክምና መዝገቦች ከህዳር 2015 በኋላ የተከሰቱ ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶችን ያሳያሉ፡ ብጥናቱ ከተካተቱት 304 መዛግብት ዉስጥ 169 ከግጭት ጋር የተገናኙ ወሲባዊ ጥቃቶች የተከሰቱት ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት ሲሆን 128 ክስተቶች ደግሞ ስምምነቱ ከመፈረሙ በኋላ ነዉ። የወሲባዊ ጥቃቶቹ ሰፋት እና አይነትም ከስምምነቱ መፈረም በኋላ ትርጉም ያለዉ ለዉጥ አላሳየም። ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት እና ጎረምሶች የተከሰቱት ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃቶች ዉስጥ 95% የሚሆኑት የተከሰቱት የሰላም ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ነው።
ተጠቂዎች ከደረሰባቸዉ ጉዳት ለማገገም የሚያሰፈልጋቸዉን የሕክምና እንክብካቤ በአስፈላጊዉ ጊዜ ማግኘት አለመቻላቸዉን መረጃዉ ያሳያል። ጥቃቱ ከተፈጸመባቸዉ ገዜ አንስቶ በጤና ተቋም የህክምና ድጋፍ እስኪያገኙ ደረስ በአማካኝ እስከ 5 ወር ድረስ ውስዶባቸዋል። የዚህን ያህል ጊዜ ሊዘገዩ የቻሉበት ምክንያቶች መገለል፤የደህንንት ስጋት፣ የግጭት መስፋፋት እንዲሁም የመጓጓዛ ትራንስፖርት መስተጉገል ልያካትቱ ሲችሉ በድርጊቱ እና ወደ ጤና ተቋም በመሄድ መካከል ያልለዉ ሰፊ የጊዜ ልዩነት አባዛኛዎቹ የተጠቁት ሴቶች እስከ አሁን ድረስ ወደ ጤና ተቋም አለምምጣታቸዉን ሊያመላክት ይችላል።

## *መደምደሚያ*

የጥቃቶቹ ብዛት፣ስርጭት እንዲሁም የወንጀለኞቹ መገለጫዎች የተከሰቱት ከግጭት ጋር የተያያዙ የወሲብ ጥቃቶች በስፋት እና በተደራጀ መልኩ መደረጋቸዉን ያመላከታል[9,10]። የጥናቱ ግኝቶች ከዚህ በፊት በጦርነቱ ዙሪያ ከወጡ ሪፖርቶች ጋር በሚመሳሰል መልኩ አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ የተለያዩ የወሲብ ጥቃቶች እንደ ጦርነትመሳሪያ፣ ዜጎችን ለማሸበር እንዲሁም አስከፊ ጥፋቶችን በሰላማዊ ዜጎች ላይ ለማድረሰ ሆን ተብለዉ መደረጋቸዉን ያሳያሉ [11-14]።

**የኢትዮጵያ እና የኤርትራ የጦር ሰራዊቶች ሰላማዊ ዜጎችን የማሰቃየት፤ማዋረድ፤ አስገድዶ መድፈር፣የወሲብ ጥቃት እና ባርነት ጨምሮ በአለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት የተደነገጉ የተለያዩ አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን፣ ኢሰብአዊ ወንጀሎችን እና የጦርነት ወንጀሎች ማድረሳቸዉን መረጃዉ ያመላክታል[15]። እነዚህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በተበዳዮቹ ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት በማድሳቸዉ አስቸኳይ የህክምና እና የስነልቦና እርዳታ ያሰፈልጋቸዋል።**

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እነዚህን ወንጀሎች እና የሰብአዊ መብት ረገጣዎች የፈጸሙትን ወንጀለኞች ተጠያቂነት በተጨባጭ ማረጋገጥ እንዲሁም ተበዳዮቹ አስፈላጉዉን የህክምና እርዳታ፣ የበደል ካሳ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ይኖርበታል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአማራ ክልል እንዲሁም በሌሎች ክልሎች ጋር ከተከሰተዉ ግጭት ጋር እንዲሁም የሰብአዊ መብት ግፎችን በመከላከል ዙሪያ ከሚነሱት ቅሬታዎች ጋር ተያይዞ ለ ጠሰቶቹ ተጠያቂነት እንደሚኖር ጠንካራ መልእክት ማስተላለፍ አሰፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል[16]። የጥናቱ ግኝቶች የጥቃቱ ሰለባዎች የደረሰባቸዉን በደል ሪፖርት እንዲያደርጉ፣ያሳለፉት አስከፊ ጊዜ እንዲመዘገብ አንዲሁም መስረጃዎች ፍትህን ለማስፈን በሚያመች ምልኩ ተሰንደዉ እንዲቀመጡ የሚያደርግተከታታይነት ያለዉ እና ከአድልዎ ነጻ የሆነ ክትትል እና ስነዳን አሰፈላጊነት የጥናቱ መረጃዎቸ በማያወላዳ መልኩ ያመልከታሉ።

## *ምክረ ሃሳቦች*

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በተኩስ አቁም ስምምነቱ መሰረት የፈትህ እንቅስቃሴዎቸ ማድረግ ቢጠበቅባትም ይህ ዘገባ እስከታተመበት ወቅት በፈትህ አተ እገባበሩ እንዲሁም ተጠያቂነትን በማስፈን ዙሪያ ለህብረተሰቡ ግልጽ የተደረጉ ማእቀፎች የሉም። የጥናታቸን ገኝቶች በኢትዮጲያ መንግስት ስ ር የተሰለፉ ሃይሎች ከተከሰተዉ ግጭት ጋር ተያይዞ የወሲብ ጥቃቶቸን መፈጸማቸዉን እና ጥቃቶቹን መቀጠላቸዉን ያመላከታል። በመሆኑም በኢትዮጵያ መንግስት በብቸኝነት የሚደረጉ ማንኛዉም ምርመራዎቸን፣ሰነዳዎችን፣እንዲሁም የፍትህ እና ተጠያቂነት እንቅሰቃሴዎችን ለመጠራጠር ከበቂ በላይ ምክንያቶች አሉ [17]። በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በመስፋፋት ላይ ካሉት ግጭቶች ጋር ተያይዞ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ስጋት በጨመረበት በአሁኑ ወቅት ይፋ የተደረጉት እነዚህ ግኝቶች የሰብአዊ መብት ክትትሎችን፣ሰነዳዎችን፣ምርመራዎችን፣ ክሶችን እንዲሁም ፍትህን በአፋጣኝ ለማረጋገጥ አለም አቀፋዊ እና ከባቢያዊ አሰራሮች አስፈላጊነትን ያረጋግጣሉ[18-19] ።

ይህ ሪፖርት ይፋ የተደረገበት የአሁኑ ሰአት የተለያዩ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህጎች እንዲሁም የተኩስ ማቆም ስምምነት ጥሰቶች መቀጠላቸዉን የሚያመላክቱ መረጃዎች ቢኖሩም የተለያዩ ነጻ የጥሰቶች ማጣርያ እና መመርመሪያ

ማእቀፎች እየተቋረጡ ያለበት ወቅት ነዉ። የተኩስ ማቆም ስምምነቱን ተከትሎ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቋቋመዉ የሰብአዊ መብት ባለሞያዎች አለም አቀፍ ኮሚሽን በኢተዮጵያ ሰራዉን መቀጠል የማይችልበት ሁኔታ ላይ እንዳይወድቅ ከባድ ስጋቶች አሉ። ኮሚሽኑ በመስከረም 2016 ዓ/ም ግኝቶቹን ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ካዉንስል እንደሚያቀርብ ቢጠበቅም የስራ ዘመኑ ከዛ ወቅት በኋላ ላይራዘም እንደሚችል የተላያዩ ምልክቶች አሉ፤ ለዚህም አንዱ ምክንያት የተለያዩ አልም አቀፍ የፍትህ እና ተጠያቂነት እንቅሰቃሴዎችን ለማቋረጥ የኢትዮጵያ መንግስት የሚያደርገዉ ጥረት ነው [20,21]። በተመሳሳይ መልኩ የአፍሪካ ህብረት የሰዎች እና ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በአትዮጵያ ዉስጥ የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመመርመር እና ወንጀለኞችን ለመለየት ያቋቋመዉ አጣሪ ኮሚሽን በኢትዮጵያ መንግስት ተቃዉሞ ደርሶበታል። ከዚህ ጋራ ተያይዞ አጣሪ ኮሚሽኑ እስካሁን ያካሄደዉን ጥናት እና ምርመራ አንዳችም ቢሆን ሪፖርት እና ምክረ ሃሳቦችን ሳያወጣ ሰራዉን አቋርጣል [22,23]።

በቀረበዉ መረጃ መሰረት ሃኪሞች ለሰብአዊ መብቶች እና ኢትዮጲያዉያን ባልደረቦቹ ለአለም አቀፍ አህጉራዊ እንዲሁም አገራዊ ተዋናዮች የሚከተሉትን ምክረሃሳቦች አቅርበዋል

1. **ከመድልዎ ነጻ የሆነ የየሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ግፎች ስነዳ እና ተጠያቂነተን መደገፍ እና ማረጋገጥ**

2. **በህጻናት እና አፍላ ወጣቶች ላይ የሚደርሱትን ጨምሮ እሰካሁን በቀጠሉት ከግጭት ጋር የተያይዙ የወሲብ ጥቃቶቸ ዙሪያ ገደብ የሌለዉ አና ቀጣይነት ያለዉ ክትትል እና ዘገባ መኖሩን ማረጋገጥ**

3. **የወሲብ ጥቃትን ጥምሮ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሰልባዎችን ፍላጎት እና አረዳድ ያካተተ እንዲሁም  ተአማኒነት እና ግልጽ መለኪያ ያለዉ የፍትህ አሰራ ማስፈን**

4. **የወሲብ ጥቃት ሰልባዎች የሰነ አእምሮ ህክምናን ጭምሮ የተለያዩ የጤና አገልገሎቶችን እንዲሁም የተለያዩ የመልሶ መቋቋም አገልግሎቶችን ያለ መድልዎ እንዲያገኙ ማሳለጥ።**

እነዚህ ምክረ ሃሳቦች እንዲተገበሩ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት እርምጃዎች በተጠቀሱት የባለ ድርሻ አካላት እንዲወሰዱ ጥሪ እናቀርባለን፡

***ለኢትየጵያ መንግስት የክልል እና የፌደራል ባለስልጣን መሰሪያቤቶች:***

- በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቋቋመዉ የሰብአዊ መብት ባለሞያዎች አልም አቀፍ ኮሚሽን በኢተዮጵያ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ያቀረባቸዉን ምክረ ሃሳቦችን (A/HRC/51/46) በአስቸኳይ ሙሉ ለሙሉ መተግበር

- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንዲሁም አለም አቀፋዊ እና ከባቢያዊ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ለሚያደርጓቸዉ ምርመራዎች በሁልም የአገሪቱ ክፍሎች እንዲንቀሳቀሱ ሙሉ ድጋፍ ማድረግ እና ጥበቃ ማድረግ

- የፍትህ ሚኒስቴር እንዲሁም ጥሰቶችን ለማረም እና ተጠያቂነት ለማስፈን የተቋቋመው የሚኒስቴሮች ግብረ ሃይል የጦር ወንጀሎችን እና የአልም አቀፍ የሰብአዊ እርዳታ ህጎችን ጨምሮ የተለያዩ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ዉስጥ ተሳትፎ የነበራቸዉን የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላትን እና አመራሮቸን ከስራ እንዲያግዱ፣እንዲመረምሩ እና ለፍትህ እንዲያቀርቡ አቅጣጫ መስጠት

- የወሲብ ጥቃት ሰልባዎች እና በሰፊዉ የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች ፍትህን ለማስፈን በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ትርጉም ባለዉ መልኩ እና ያለ ምንም ሰጋት መሳተፋቸዉን ማረጋገጥ እንዲሁም ለደህንነታቸዉ እና ፍላጎታቸዉ ቅድሚያ መስጠት።

- የተለያዩ የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ከግጭት ጋር የተያያዙ የወሲብ ጥቃቶች ሰለባዎች የህክምና አገልግሎቶችን ጨምሮ ገደብ የሌለዉ የሰብአዊ እርዳታ ያለመገለል እንዲያገኙ መፍቀድ

- የተከሰቱት ጥሰቶች አሰፈላጊዉ የእርምት እርምጃ እና ካሳ መሰጠቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ከግጭት ጋር የተያያዙ የወሲብ ጥቃቶች ሰለባዎች      ሚስጥራዊቱን እና ደህንነቱን በጠበቀ መልኩ ነጻ እና በቂ የህክምና፣የሰነ ልቦና እና የህግ አገልግሎቶችን ያለመገለል እንዲያገኙ ማድረግ

***የኢትዮጵያ እና የኤርትራ መንግስቶችን ጨምሮ ለሁሉም የግጭቱ ተሳታፊዎች:***

○ የአልም አቀፍ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊ እርዳታ ህጎች ላይ እንዲሁም የተኩስ ማቆም ስምምነቱ ላይ በተደነገገዉ መሰረት የማሰቃየት፣ማዋረድ፣ አስገድዶ መድፈር፣የወሲብ ጥቃት እና ባርነት ጨምሮ ማንኛዉም የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ማቆም እና ሰላማዊ ዜጎችን የመጠበቅ ግዴታቸዉን መወጣት

○ ማንኘዉም አይነት የጾታና የወሲብ ጥቃቶች በግልጽ ማዉገዝ ፣በአስቸኳይ እንዲቆሙ ትእዛዞችን ማስተላለፍ እንዲሁም የጥሰቶቹን ምርመራዎች እና ክሶችን በማሳለጥ ለተበዳዮች ፍትህ መቆም

○ ከአልም አቀፍ ህግ ጥሰቶች ተጠያቂነት ከለላን ከሚደረጉት ማንኛቸዉም የሰላም ስምምነቶች ዉስጥ አለማካተት

○ ሰላማዊ ዜጎችን ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ የሰብአዊ እርዳታ አገልግሎቶችን እና አቅርቦቶችን እንዲያገኙ መፈቀድ እና ማመቻቸት

***ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ:***

- በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቋቋመዉ የሰብአዊ መብት ባለሞያዎች አለም አቀፍ ኮሚሽን በኢተዮጵያ እንዲራዘም መደገፍ

- ጦርነቱ ከተጀመረበት ግዜ አንስቶ የተከሰቱ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እና የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግ ጥሰቶች ዙርያ በአስፈላጊዉን የፋይናንስ ግብአት የተደራጀ፣ተከታታይ እና ከጣልቃ ገብነት ነጻ የሆኑ ዘገባዎች እና የመረጃ ስርአቶች መዘርጋታቸዉን ማረጋገጥ። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቋቋመዉ የሰብአዊ መብት ባለሞያዎች አለም አቀፍ ኮሚሽን በኢተዮጵያ የማይራዘምበት ሁኔታ ከተፈጠረ ኮሚሽኑ የለያቸዉን መረጃዎች እና ማስረጃዎች ታቅበዉ እንዲቆዩ ማድረግ እና ከኮሚሽኑ ጋር ተመጣጣኝ ስልጣን ያለዉ አጣሪ አካል እንዲሰየም ማድረግ

- እስካሁን በኢትዮጵያ በተደረጉ ጥናቶች የተጠቆሙትን አስከፊ የአለም አቀፍ የሲብአዊ መብት ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲጣሩ እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማስቻል

- ከሰብአዊ እርዳታ እና ድጋፍ ዉጪ ለኢትዮጵያ መንገስት የሚደረጉ የገንዘብ ደጋፎችን መንግስት ፍተህ እና ተጠያቂነትን ለማስፈን በመሚያደርጋቸዉ ተጨባጭ ጥረቶች እና በዚህ ዙሪያ ባለዉ የህበረተሰብ ተቀባይነት ዙሪያ የተመሰረተ ማድረግ

- በተኩስ ማቆም ስምምነቱ ላይ የተጠቀሱ ግዴታዎች እና ትግበራዎች በአግባቡ መተግበራቸዉን መከታተል እና ማረጋገጥ

- አገር በቀል የፍተህ እና ተጠያቂነት አሰራሮችን ግልጽ፣ ከአድልዎ ነጻ ከጣልቃ ገብነት ነጻ እንዲሁም የሰለባዉቹን ተሳታፊነት ያካተቱ መሆናቸዉን ማረጋገጥ እና የነሱ የመሳተፍ መብት እና ደህንነት ማስጠበቅ

- በተለያዩ ባለሞያዎች ማለትም በፍትህ፣በህግ ጠባቂ እና በጤና ባለሞያዎች በአሸጋጋሪ ፍትህ ዙሪያ ያላቸዉን እውቀት እንዲያካብቱ እንዲሁም ምርመራዎችን እና ክሶችን መደገፍ የሚችሉበትን አሰራር በቴክኒክ እና በ ገንዘብ መደገፍ

- የጥቃት ተጎጂዎችን እና ሰለባዎቸን ማእከል ያደረገ እንክብካቤ እና የመልሶ ማቋቋም ሰራዎችን ቅድሚያ መስጠት እንዲሁም ህጻናት እና አፍላ ወጣቶች በልዩ ሁኔታ እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ

***በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የጋራ ቡድን:***

- ሁሉም የግጭቱ ተሳታፊዎች የጋራ ቡድኑ በ2014 ዓ/ም ባወጣዉ ሪፖርት በተለይም በተራ ቅጥር 5 እና 6 ያካተታቸዉን ምክረ ሃሳቦች ማለትም “ሰላማዊ ሰዎች ላይ በዘር ማንነት ላይ ተመስርተዉ የሚደረጉ ጥቃቶቸን ጨምሮ ሁሉንም አይነት በሴቶች በወንዶች እና በህጻናት ላይ የሚደረጉ የወሲብ ጥቃቶችን ማስቆም ” እንዲሁም “ የወሲብ እና የጾታ ጥቃቶችን መፈጸም በቀጥታ እና ከእዝ ሰንሰለት ግዴታ ጋር ተያይዞ እንደሚያሰቀጣ ለሁሉም ታጠቂ ሃይሎች እና ቡድኖች እንዲሁም አመራሮች ግልጽ እና የማያወላዳ አቅጣጫ ማስቀመጥ” የሚሉትን መተግበራቸዉን ማረጋገጥ።

***ለአፍሪካ ህብረት የሰዎች እና ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን:***

- ህብረቱ ያቋቋመዉን የሰብአዊ መብት አጣሪ ኮሚሽን ለመበተን የደረሰባትን ዉሳኔ በአስቸኳይ በ ድጋሚ እንዲመረምረዉ እና የአጣሪ ኮሚሽኑን ግኝቶች ይፋ ማድረግ።

## References


1. Cessation of Hostilities Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Tigray Peoples' Liberation Front (TPLF) - Ethiopia | ReliefWeb. Published November 3, 2022. Accessed June 14, 2023. https://reliefweb.int/report/ethiopia/cessation-hostilities-agreement-between-government-federal-democratic-republic-ethiopia-and-tigray-peoples-liberation-front-tplf
2. Human Rights Watch. Ethiopia: Ethnic Cleansing Persists Under Tigray Truce. Published online June 1, 2023. Accessed August 2, 2023. https://www.hrw.org/news/2023/06/01/ethiopia-ethnic-cleansing-persists-under-tigray-truce
3. Ethiopia war in Tigray: Eritrean soldiers accused of rape despite peace deal. *BBC News*. https://www.bbc.com/news/world-africa-64635898. Published February 15, 2023. Accessed August 2, 2023.
4. International Criminal Court. *Elements of Crimes*.; 2013. Accessed June 29, 2023. https://www.icc-cpi.int/sites/default/files/Publications/Elements-of-Crimes.pdf
5. Woldemikael TM. Language, Education, and Public Policy in Eritrea. *African Studies Review*. 2003;46(1):117-136. doi:10.2307/1514983
6. Ado D, Gelagay AW, Johannessen JB. *Grammatical and Sociolinguistic Aspects of Ethiopian Languages*. John Benjamins Publishing Company; 2021.
7. Translators without Borders. Language data for Ethiopia. Translators without Borders. Accessed June 29, 2023. https://translatorswithoutborders.org/language-data-for-ethiopia/
8. Dahir AL, Marks S. Slaughter on Eve of Ethiopian Peace Draws Accusations of War Crimes. *The New York Times*. https://www.nytimes.com/2023/03/01/world/africa/eritrea-ethiopia-tigray-war.html. Published March 1, 2023. Accessed August 7, 2023.
9. Trendafilova JE, Kaul JHP, Tarfusser JC. Decision Pursuant to Article 15 of the Rome Statute on the Authorization of an Investigation into the Situation in the Republic of Kenya. Published online March 31, 2010.
10. Aranburu XA. Sexual Violence beyond Reasonable Doubt: Using Pattern Evidence and Analysis for International Cases. *Leiden Journal of International Law*. 2010;23(3):609-627. doi:10.1017/S0922156510000245
11. OHCHR, International Commission of Human Rights Experts on Ethiopia. *Report of the International Commission of Human Rights Experts on Ethiopia*. Human Rights Council, Fifty-first session; 2022. Accessed January 27, 2023. https://www.ohchr.org/en/hr-bodies/hrc/ichre-ethiopa/index
12. Amnesty International. *Ethiopia: "I Don't Know If They Realized I Was a Person": Rape and Sexual Violence in the Conflict in Tigray, Ethiopia*. Amnesty International; 2021. Accessed January 11, 2023. https://www.amnesty.org/en/documents/afr25/4569/2021/en/
13. *"We Will Erase You from This Land": Crimes Against Humanity and Ethnic Cleansing in Ethiopia's Western Tigray Zone*. Human Rights Watch; 2022. Accessed June 21, 2022. https://www.hrw.org/report/2022/04/06/we-will-erase-you-land/crimes-against-humanity-and-ethnic-cleansing-ethiopias
14. War Crimes, Crimes Against Humanity, and Ethnic Cleansing in Ethiopia. United States Department of State. Accessed June 27, 2023. https://www.state.gov/war-crimes-crimes-against-humanity-and-ethnic-cleansing-in-ethiopia/
15. International Criminal Court. Rome Statue of the International Criminal Court. Published online 1998. Accessed May 23, 2023. https://www.icc-cpi.int/sites/default/files/RS-Eng.pdf
16. International Commission of Human Rights Experts on Ethiopia. Statement attributable to the International Commission of Human Rights Experts on Ethiopia on the security situation in the north-west. Published online August 10, 2023. Accessed August 11, 2023.

https://www.ohchr.org/en/statements/2023/08/statement-attributable-international-commission-human-rights-experts-ethiopia
17. Ibrahim A. The Ethiopian Human Rights Commission: A Champion of Transitional Justice? *Harvard Law School | Human Rights Program*. Published online August 4, 2023. Accessed August 11, 2023. https://hrp.law.harvard.edu/the-ethiopian-human-rights-commission-a-champion-of-transitional-justice/
18. Reports of Mass Atrocities in Western Tigray. United States Department of State. Accessed August 7, 2023. https://www.state.gov/reports-of-mass-atrocities-in-western-tigray/
19. Multiple injuries as Ethiopian military, militia clash in Amhara: Sources | Conflict News | Al Jazeera. Accessed August 7, 2023. https://www.aljazeera.com/news/2023/8/2/ethiopian-military-clashes-with-militia-in-amhara-injuries-reported
20. Endale A. Ethiopia Demands Termination Of Mandate For UN Rights Experts | The Reporter | Latest Ethiopian News Today. *The Reporter*. https://www.thereporterethiopia.com/28639/. Published December 17, 2022. Accessed August 8, 2023.
21. Ethiopia: Government's effort to end mandate of UN human rights commission must be rejected. Amnesty International. Published March 3, 2023. Accessed August 6, 2023. https://www.amnesty.org/en/latest/press-release/2023/03/ethiopia-governments-effort-to-end-mandate-of-un-human-rights-commission-must-be-rejected/
22. Threats to Terminate the Mandate of the International Commission of Human Rights Experts on Ethiopia. Human Rights Watch. Published February 28, 2023. Accessed August 8, 2023. https://www.hrw.org/news/2023/02/28/threats-terminate-mandate-international-commission-human-rights-experts-ethiopia
23. Standard A. News: AU rights commission quietly liquidates inquiry on Tigray, removes trace of page from website. Addis Standard. Published July 11, 2023. Accessed August 8, 2023. https://addisstandard.com/news-au-rights-commission-quietly-liquidates-inquiry-on-tigray-removes-trace-of-page-from-website/